United We **Prepare**

UNITED WAY Southern Nevada | verizon

ቤተሰባችን
የአደጋ ዝግጅት እቅድ

የቤተሰብ መረጃ

የቤተሰብ ሐላፊ(ዎች) ስም(ስሞች)፦ _____

አድራሻ፦ _____

የስልክ ቁጥር(ሮች)፦ _____

ኢሜይል፦ _____

የቤተሰብ መሰብሰብያ ቦታ

ከተለያየን የምንገናኝበት ቦታ፦

በአቅራቢያው የሚገኝ ቦታ፦ _____

ለምሳሌ፦ በአያቴ ጓሮ ውስጥ ባለው የማቆሚያ ምልክት ላይ

ከአካባቢው ውጪ የሚገኝ ቦታ፦ _____

ለምሳሌ፡ - በአጎቴ John ቤት

ምክር፦ የNevada ትራፊክ መጨናነቅ እና በጎርፍ የተጥለቀለቁ ጎዳናዎችን በበይነ መረብ በቀጥታ ይዩ **www.nvroads.com**

የጥገናችን እቅድ

ለመጨረሻ ጊዜ የጉዞ ቦርሳችን የፈተሸነው፦ ____/____/____

የምንፈትሸው/የምናሳድሰው በ፦ ____/____/____

ምክር፦ ማስታወሻ ወደ የቀን መቁጠሪያዎ ያጨምሩ!

UNITED WAY Southern Nevada | 211 Get Connected. Get Help.®

ከአደጋ በፊት፣ በአደጋ ጊዜ ወይም ከአደጋ በኋላ እርዳታ ለማግኘት ወደ 211 ይደውሉ። 24/7/365 ክፍት ነው።

ከአደጋ በፊት **መዘጋጀት**

የድንገተኛ አደጋ ተጠሪዎች + አስፈላጊ ስልክ ቁጥሮች

አማራጭ፦ ተመሳሳይ የእውቂያ ዝርዝር በበይነ መረብ ለመሙላት QR ኮድን ስካን ያድርጉ፤ ከዛ አውርደው ያትሙት።

የአደጋ ጊዜ ተጠሪ (ከከተማ ውጭ)፦
ስም፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

በአከባቢ የሚገኝ የአደጋ ግዜ ተጠሪ (ጎረቤት/ጓደኛ)፦
ስም፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የመጀመሪያ ሐኪም/ክሊኒክ፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የሕፃናት ሐኪም፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

መድሐኒት ቤት፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

ባንክ፦ _____
በቅርብ የሚገኝ ቅርንጫፍ አድራሻ፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የህክምና መድህን አቅራቢ
የፖሊሲ ቁጥር፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የቤት/የተከራዮች መድህን ሰጪ፦
የፖሊሲ ቁጥር፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የመኪና መድህን፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

ትምህርት ቤት/የልጅ እንክብካቤ፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የአዋቂዎች እንክብካቤ ተቋም፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

የእንስሳት ሐኪም (Veterinarian)፦ _____
ስልክ ቁጥር፦ _____

ምክር፦ የዚህን ስልክ ዝርዝር ቅጂ ለሌሎችም ይስጡ!

ምክር፦ ድንገተኛ አደጋዎች፣ በተለይ ለአረጋውያን እና ለአካል ጉዳተኞች ፈታኝ ሊሆኑ ይችላሉ። ደህንነትዎ ለመጠበቅ እና የሚያስፈልግዎት ነገሮችን ለማሟላት ከሁሉ የተሻለ የግል የአደጋ ጊዜ እቅድ ማውጣት ነው። ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ የሚጠቅም እቅድ ለመፍጠር፣ የሚከተለውን ድህረ ገጽ በመጎብኘት የሚያስፈልግዎትን ሁሉንም መረጃ ያግኙ **bereadynv.org**

በቤቴ የሚኖረው ማን ነው?

ይህ ክፍል ለሁሉም ይመከራል፤ በተለይ ደሞ፣ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ላልሆኑ ወይ ደሞ ከድንገተኛ አደጋ ባለስልጣናት ጋር የመነጋገ ችግር ላለባቸው ሌሎች። ከ ___/___/ ጀምሮ

ስም	ዕድሜ	የምግብ እና የመድኃኒት አለርጂ	ልዩ የድጋፍ ፍላጎት፣ የመድሐኒት መጠን

የቤት እንስሳት ስም	ዝርያ	ልዩ ፍላጎቶች እና ማስታወሻዎች

ከአደጋ በፊት **መዘጋጀት**

የአደጋ ጊዜ የጉዞ ቦርሳዎ ያሽጉ!

በጣም አስፈላጊ ነገር እቃዎች "ሊኖሩት ይገባል"

- ☐ የሁሉም ሰው እና የቤትዎ፣ የውስጥ እና የውጭ ወቅታዊ ፎቶዎች (ወይም በስማርት ስልክዎ ላይ ያስቀምጧቸው)
- ☐ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የጉዞ ቦርሳ መለያ መሰየም
- ☐ የማይበላሽ እንዲሁም ማቀዝቀዣ፣ ቅመሞች እና እቃዎች የማይፈልግ ምግብ (የ 3 ቀን አቅርቦት በሰው)
- ☐ ጠቃሚ ሰነዶች የሚቀመጡበት ወሃ የማያስገባ ቦርሳ/መያዣ
- ☐ ማንኪያዎች፣ መልሰህ መጠቀም የሚቻል
- ☐ የሚለበስ የዝናብ መከላከያ
- ☐ በእጅ የሚሰራ የጣሳ መክፈቻ
- ☐ ለ 5 - 7 ቀናት የሚሆን የወሃ አቅርቦት (1 ጋሎን በሰው በቀን)
- ☐ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሆን ልብስ ቅያሬ (ብያንስ ካልሲዎች እና የውስጥ ልብሶች)
- ☐ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች (7–14 ቀን አቅርቦት/ሰው)
- ☐ ማቀዝቀዣ ውስጥ መቆየት ለሚያስፈልጋቸው መድሃኒቶች፣ ፈጣን ቀዝቃዛ ማሸጊያዎች
- ☐ በሃኪም ያልታዘዙ መድሓኒቶች ያለበት የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ
- ☐ የመነጽር መለዋወጫ፣ እውቂያዎች
- ☐ የሚታጠፍ፣ በእጅ የሚያዝ የአየር ማቀዝቀዣ
- ☐ ለጉዞ የሚሆኑ የንጽህና ዕቃዎች (ሳሙና፣ የጥርስ ብሩሽ፣ ወዘተ)
- ☐ የሽንት ቤት ጥቅል ወረቀቶች
- ☐ ከፕላስቲክ የተሰራ፣ ጠንካራ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ
- ☐ በፀሐይ ወይም በባትሪ ኃይል የሚሰራ ሬድዮ/የእጅ ባትሪ
- ☐ ተጨማሪ ባትሪዎች፣ ኃይል ባንኮች ቻርጅ ማድረግያ ገመዶች
- ☐ የማይጠፋ ምልክት ማድረግያ፣ ወረቀት እና እርሳስ
- ☐ የአደጋ ጊዜ ፊሽካ
- ☐ መገልገያዎች ለማጥፋት የሚሆን ቁልፍ ወይም ለብዙ የሚያገለግል መሳሪያ
- ☐ ፀረ-ተባይ
- ☐ የመጸዳጃ ወረቀት
- ☐ ጥቁር ፕላስተር

ሌሎች እቃዎች

- ☐ የቀዝቃዛ አየር ሁኔታ መሳሪያ፦ የmylar ብርድ ልብሶች እና እጅ ማሞቅያዎች
- ☐ የሞቃታማ የአየር ሁኔታ መሣሪያ፦ የፀሐይ መከላከያ እና ለጥላ የሚሆን ጃንጥላ
- ☐ ውሃ የማያስገቡ ክብሪቶች፣ ማቀጣጠሊያ
- ☐ ፀረ-ተባይ
- ☐ ጥሬ ገንዘብ
- ☐ የስራ ጓንት
- ☐ የካርድ ዴክ፣ የልጆች መጫወቻ
- ☐ የሚያንጸባርቁ ማሰሪያዎች/አልባሳት
- ☐ ለአዋቂዎች የሚሆን ሽንት ወይም ሰገራ የምያምቁ የውስጥ ልብሶች
- ☐ የህጻን ምግብ እና አቅርቦቶች (አስፈላጊ ከሆነ)
- ☐ የቤት እንስሳት ምግብ እና መድኃኒት፣ ትርፍ መያዣ ገመድ እና ተሳቢ

የጠቃሚ ሰነዶች ቅጂ ይያዙ ወይም ይተኩ

ሁሉም አስፈላጊ ሰነዶች የሚገኝበት ውሃ የማይገባበት ቦርሳችን የሚገኘው፦

_____

_____

ለምሳሌ፦ በጉዞ ቦርሳችን ውስጥ!

ጠቃሚ፦ የሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶች ዲጂታል ቅጂዎች በUSB drive ላይ ያስቀምጡ እና በጉዞ ቦርሳዎ ውስጥ ያከማቹ፤ ወይም የ Wi-Fi ኔትወርክ ስታገኙ ከየትኛውም ቦታ ተደራሽ እንዲሆኑ በ cloud storage ውስጥ ያስቀምጡ።

ሌሎች ሰነዶች

- የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የግል ፎቶዎች (ጉርድ ፎቶዎች)
- የቤት እቃዎች (ከእንጨት የተሰሩ ዕቃዎች፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ተሸከርካሪዎች፣ ወዘተ ጨምሮ ሁሉንም ውድ ዕቃዎች ይዘርዝሩ)
- የኮንትራት/ኪራይ ስምምነት
- የመድህን ፖሊሲዎች (የቤት፣ የተከራይ፣ የመኪና፣ የቤት እንስሳ)
- የዚህ ሙሉ የአደጋ እቅድ ፎቶ አንሱ

የፌደራል ሰነዶች

ማህበራዊ ዋስትና ካርዶች
- SSA.gov ወይም 800-772-1213 (TTY 800-325-0778)

የMedicare ካርዶች
- Medicare.gov ወይም 800-633-4227 (TTY 877-486-2048)

ፓስፖርት
- Pptform.state.gov ወይም 877-487-2778 (TTY 888-874-7793)

የቋሚ ነዋሪነት ካርድ (ግሪን ካርዶች)
- myaccount.uscis.gov ወይም 888-897-7781 (TTY 877-875-6028)

የውትድርና መዝገቦች
- archives.gov/veterans

የግዛት እና የአውራጃ ሰነዶች

የልደት እና የሞት የምስክር ወረቀቶች፣ የጋብቻ እና የፍቺ ቅጂዎች (የተረጋገጠ እና ያልተረጋገጠ)
- dhhs.nv.gov
- ወይም ለተመዘገቡበት አውራጃ ጽሕፈት ቤት ያነጋግሩ

የNevada መንጃ ፈቃድ (Nevada Driver's License) ወይም የፎቶ ያለው መታወቂያ ካርድ
- dmv.nv.gov

የመኖሪያ እና የንብረት መዝገቦች

የአድራሻ/የመኖርያ ማረጋገጫ፦
የቅርብ ጊዜ ሂሳብ ለማግኘት የፍጆታ ኩባንያዎን ያነጋግሩ
- ለNV ሐይል፦ 702-402-5555
- ለSouthwest ነዳጅ፦ 877-860-6020
- የLas Vegas Valley አውራጃ ወሃ፦ 800-252-2011

የሪል እስቴት እና የንብረት መዝገቦች፦
የንብረት ክፍያ ድርጅትዎ (mortgage company) ወይም የአውራጃዎ ገምጋሚ ቢሮ ያነጋግሩ

የፋይናንስ ደህንነት ምክሮች፦
- የክፍያ መዘግየትን ለማስቀረት ወደ ቀጥታ ተቀማጭ ገንዘብ መቀየር
- የሚከፍሉትን ማንኛውንም የሂሳብ ክፍያ መግለጫ (የኪራይ፣ የመገልገያዎች ፣ የብድሮች፣ የምዝገባዎች) በቀጥታ ማውረድ ወይም ማተም
- በስማርት ስልክዎ ላይ ማንኛውንም የባንክ ወይም የሂሳብ ክፍያ የሞባይል መተግበሪያዎችን ማውረድ

የመጀመሪያ እርምጃዎች ከአደጋ በኋላ

UNITED WAY Southern Nevada | 211 Get Connected. Get Help.®

ለእርስዎ...

ቤተሰብዎ

- ያሉትን የገንዘብ እንዲሁም ሌሎች የእርዳታ ምንጮችን ይዘርዝሩ
- መተካት የሚያስፈልጉዎትን ነገሮች ይዘርዝሩ
- የደረሰውን ጉዳት ፎቶ ያንሱ
- ከቤተሰብዎ እና ጓደኞችዎ ጋር ግንኙነትዎ አይቋረጥ
- ድጋፍ ቡድን ለመቀላቀል ግምት ውስጥ ያስታውሱ።
- የተለመዱት ተግባራትን በፍጥነት ድጋሜ ይጀምሩ
- ሁሉም ስለ ስሜታቸው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው፤ ስለራስዎ ሐቀኛ ይሁኑ

እራስዎ

- በአግባቡ ተመገቡ እና ብዙ ውሃ ጠጡ
- ውጥረትን ለመቀነስ የአካል እንቅስቃሴ ያድርጉ – ፈጠን ያለ የእግር ጉዞ ያድርጉ
- ከመጠን በላይ አያድርጉት እና ብዙ እረፍት ያድርጉ – መተኛት ካልቻሉ ትንሽ እንቅልፍ ይተኙ
- ስለ ፍርሃቶችዎ እና ስጋቶችዎ ይናገሩ፤ ጭንቀትዎን ለመቆጣጠር ከሚረዳዎ አማካሪ ጋር መነጋገርን ያስቡበት እና በሚፈልጉበት ጊዜ እርዳታ ለመጠየቅ አያመንቱ።

ልጆችዎ

- ብዙ የሚያጽናና እቅፍ ይስጡዋቸው
- ተጨባጭ የአደጋ መረጃ ይስጡዋቸው
- በመኝታ ሰዓት አብረዋቸው ተጨማሪ ጊዜ አሳልፉ
- ልጆቻችሁን ልዩ የቤት ስራ በመስጠት በማገገም ላይ ያሳትፉ
- ኃላፊነት የሚሰማውን ባህሪ ያወድሱ

ቤትዎ/አፓርታማዎ

- ከመመለስዎ በፊት ቤትዎ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጡ
- የመድህንዎ ወኪል ያግኙ – ሸፋንዎን አይገምቱ
- ከአንድ በላይ የጥገና ግምት ያግኙ
- ደረሰኞችን በአስተማማኝ ቦታ ያስቀምጡ
- በራስዎ ወይም በሌሎች እርዳታ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ይወስኑ
- ባለሙያ የምያስፈልገውን ነገር ይወስኑ (ኤሌክትሪካል፣ ቧምቧ)
- በማጣቀሻዎች አማካኝነት ተቋራጮችን ያረጋግጡ

ማቀዝቀዣ ጣቢያ ያግኙ

- allin.clarkcountynv.gov/Initiative/StayCool

የመጀመሪያ የስልክ ጥሪዎች

- የተማሪው መውጫ ሂደቶችን ለመፈተሽ ወደ ትምህርት ቤት/የህፃናት ማቆያ ማእከላት
- በዕድሜ የገፉ የቤተሰብ አባላትን ለመፈተሽ እርዳታ ለሚደረግላቸው የመኖሪያ/የአረጋውያን ቤቶች መደወል
- ጎረቤቶችዎ ለመፈተሽ ወደ ቤቶቻቸው መሄድ እና የሚችሉ ከሆነ እርዳታ ይስጡ

የህግ አገልግሎቶች

የተከራይነትዎ መብቶች ማወቅ፣ **www.lacsn.org**

የSouthern Nevada የህግ እርዳታ ማእከል (Legal Aid Center of Southern Nevada) በአከራዮች፣ በጠፉ ህጋዊ ወረቀቶች እና የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ልያግዝ ይችላል። ወደ 702-386-1070 ይደውሉ

የተጎዳ ንብረት ካለዎት...

1. ቤትዎ ከውስጥም ከውጭም **ፎቶዎች** ያንሱ።
2. ሸፋንን ለማረጋገጥ ወደ መድህን ድርጅትዎ ይደውሉ
3. የተበላሹ ቁሳቁሶችን ከቤትዎ እንዴት **እንደሚጸዱ እና እንደሚወገዱ** - ይህንን የ 3 ደቂቃ ቪዲዮ ይመልከቱ
   - ከመሻገቱ በፊት ይጀምሩ
   - መገልገያዎችን ይዝጉ
   - ንብረቶችዎ ያጽዱ
   - በመግቢያዎች፣ በመስኮቶች እና መሰረቶች አከባቢ ያለውን የተቆራረጠ ውኃ መስመሮች ያስወግዱ
   - ከወለል እስከ 4 ጫማ (1.2 ሜትር) ድረስ ያለውን ደረቅ ግድግዳ ያስወግዱ (ምንም እንኳን የውኃው መስመር እስከ 4 ጫማ ምልክት ድረስ የማይደርስ ቢሆንም)
   - መከላከያን ያስወግዱ
   - ቤትዎ ያጽዱ እና ያድርቁ
4. **ፍርስራሾች** በተለያዩ የግንባታ እቃዎች ክምሮች እና የተፈጥሮ/አረንጓዴ ቆሻሻ ይለያዩ እና በመንገድ አጠገብ (መንገድ ውስጥ አይደለም) ያስቀምጡ

የምግብ ባንክ ያግኙ

- nevada211.org

ልዩነቱ ይወቁ

- **911** - ድንገተኛ አደጋዎች ሕይወት አድን
- **211** - ከማህበራዊ አገልግሎቶች እና ሌሎች ሀብቶች ጋር ለመገናኘት(24/7)
- **311** - የረብሻ ጥሪ፣ አጠራጣሪ እንቅስቃሴ፣ ያለፉ ወንጀሎች፣ የትራፊክ እና ሌሎች ስጋቶች
- **988** -የራስን ማጥፋት/የቀውስ መስመር (መደወል ወይም የጽሑፍ መልእክት መላክ)

FEMA እና SBA

አደጋው በፌዴራል ደረጃ በUnited States ፕሬዚዳንት የታወጀ ከሆነ፣ የFEMA እና SBA ሃብቶች ከአደጋው ለተረፉ ሰዎች ሊሰጥ ይችላሉ።

የፌዴራል የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ኤጀንሲ (Federal Emergency Management Agency, FEMA)

- ገንዘቦችን የመሸለም እድሎችዎን ለመጨመር፣ የFEMA ማመልከቻዎን ለመሙላት የFEMA የአደጋ ምንጭ ማዕከል (FEMA Disaster Resource Center (DRC)) **በአካል** ይጎብኙ
- **በመጀመሪያው ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገብዎት፣ ሁልጊዜ ውድቅ የተደረገበትን ደብዳቤ ይግባኝ ይበሉ**
- እዚህ ይጀምሩ፦ disasterassistance.gov

የአነስተኛ ንግድ አስተዳደር (Small Business Administration (SBA))

SBA (የአነስተኛ ንግድ አስተዳደር) ግለሰቦች፣ የቤት ባለቤቶችን እና ተከራዮችን (ትናንሽ ንግዶችን ብቻ አይደለም) በዝቅተኛ ወለድ በሚሰጡ ብድሮች በኩል ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለሚከተሉት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፦

- በታወጀ አደጋ የተበላሹ በኢንሹራንስ ወይም በFEMA የማይሸፈኑ አካላዊ ንብረቶችን ለመጠገን እና ለመተካት
- ወደፊት የሚደርስ ጉዳትን ለመቀነስ/ለማስወገድ የማቅለያ እገዛ (ምሳሌ፦ የFrench ፍሳሽ ማስወገጃ መትከል ወይም የቤትዎን የአየር ሁኔታ ማስተካከል)
- እዚህ ይጀምሩ፦ sba.gov/disaster